# ስለ ዕድ ያለመክፈል ክስ መዝገብዎ ነፃ ጠበቃ ማዋራት ይችላሉ



## ጠበቃን እንዴት ማግኘት እችላለሁኝ?

- ጠበቃ እንደሚፈልጉ ለዳኛው ይንገሯቸው፣ ወይም
- የዲሲ የዕዳ መሰብሰብ (DC Debt Collection) ስልክ መስመር (202) 851-3387 ላይ ይደውሉ።



## ጠበቃን ማነጋገር ለምን ያስፈልገኛል?

ብዙ ምክንያቶች አሉ። አንዳንዶቹ ምክንያቶች፡-

- ስለ የዕዳ ያለመክፈል የክስ መዝገብዎ የበለጠ ማወቅ ሲፈልጉ ወይም ክሱ ጭንቀት የሚፈጥርብዎ ከሆነ።
- ዕዳ የለብኝም ብለው የሚያስቡ ከሆነ። ወይም አካውንቱን የማያውቁት ከሆነ።
- መክፈል እየፈለጉ አሁን ሁሉንም በአንዴ መክፈል ካልቻሉ።
- ገንዘብዎን የሚያገኙት ከሚከተሉት ጥቅማጥቅሞች ከሆነ፡-
  - ጡረታ (እንደ ማህበራዊ ደህንነት) - የአካለስንኩልነት (እንደ SSI ወይም SSDI)
  - TANF – የልጅ ድጎማ
  - የሠራተኞች ካሣ -የሥራ አጥነት
- የክስ መዝገብዎ የመኪና አደጋ የሚያካትት ከሆነ፣ እና የሌላኛው መኪና ስህተት ከነበረ። ወይም ኢንሹራንስ ያለዎት ከሆነ።
- ክስ የሚሰማበት ቀን ላይ ካልተገኙ። ወይም በእርስዎ ላይ የተፈረደብዎ ከሆነ።
- ክስዎ በሽምግልና እንዲፈታ ቀጠሮ ከተያዘለት። *ስለ ሽምግልና የበለጠ መረጃ ቀጣዩ ገጽ ላይ ይገኛል።*

Legal Aid Society OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MAKING JUSTICE REAL

TZEDEK DC
Legal Help for People in Debt

# ቀጠሮ የተያዘለት ሽምግልና ያሎት ከሆነ፡-
## መብትዎን ይወቁ እና ምን መጠበቅ እንዳለብዎ።

### ሽምግልና ምን ማለት ነው?

1. ሽምግልና በእርስዎ፣ እርስዎን በሚከሰው ኩባንያ፣ እና በሽምጋይ መካከል የሚደረግ ስብሰባ ነው። ሽምጋዩ ለሁሉቱም ወገኖች ወግኖ አይሰራም።



### ሽምግልና ላይ ምን ይፈጠራል?

1. ያለ ፍርድ ቤት ክስ መዝገብ ጉዳዮን በስምምነት ሊፈቱ ይችላሉ። ነገር ግን ማንኛውም ነገር ላይ የመስማማት ግዴታ የለብዎትም።

2. በሽምግልና ወቅት ሌላኛውን ወገን መረጃ እንዲሰጥዎ የመጠየቅ መብት አሎት። ብዙ ጊዜ የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ ከፍርድ ቤት ክስ ይልቅ የሽምግልና መንገድ እንደሚመርጡ ለሽምጋዩ ይናገሩ።

3. የክፍያ ዕቅድ እንዲሰጥዎ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ውሎቹ ላይ መደራደር ይችላሉ። ለምሳሌ፡-

    - ለመክፈል የተስማሙት አጠቃላይ የገንዘብ መጠን።
    - እያንዳንዱ ወር ላይ ምን ያህል እንደሚከፍሉ።
    - ክፍያዎ መቼ እንደሚከፈሉ




### ስለ ክፍያ ዕቅዶች ምን ማወቅ ይጠበቅብኛል?

1. ለመክፈል የተስማሙበትን ማንኛውም ክፍያ መክፈል እንደሚችሉ ያረጋግጡ።  ጊዜው ሲደርስ መክፈል እንደሚችሉ ያረጋግጡ።

2. የክፍያ ዕቅድ ላይ የሚስማሙ ከሆነ እና በተስማማቹበት መሰረት የማይከፍሉ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በእርስዎ ላይ ሊፈርድ ይችላል። ያ ከሳሹ ከደሞዝዎ ወይም ከባንክ አካውንትዎ ላይ ገንዘብ መውሰድ እንዲችል ሊያስችለው ይችላል።

3. የመንግስት ጥቅማጥቅሞች የሚያገኙ ከሆነ፣ ለመክፈል ከመስማማትዎ በፊት ጠበቃ ያነጋግሩ።   ሕጉ አብዛኛዎቹን ጥቅማጥቅሞች ከዕዳ ሰብሳቢዎች ይጠብቃል።

**ከሽምግልና በፊት *በነፃ* ጠበቃ ያነጋግሩ። (202) 851-3387 ላይ ይደውሉ።**

*ይሄ መረጃ የተዘጋጀው በዲስ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ዕዳ ባለመክፈላቸው ምክንያት ለተከሰሱ ሰዎች ነው።  መረጃው የሕግ ምክር አይደለም።*